እምሩ ዘለቀ፤ *ጉዞ፣ የሕይወቴ ትውስታ*፤ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ 2015 (ከእንግሊዝኛው የተመለሰ)፣ 382 ገጽ።

ቀደም ባሉት ዓመታት በኢትዮጵያውያን ዘንድ ግለ ታሪክንና ትውስታን ጽፎ ለአንባቢ ማካፈል የተለመደ አልነበረም። ይህን ለማድረግ የሞከሩት ፊር ቀዳጅ ደራስያንም ቅጥ ያጣ ትችትና ዘለፋ እንደወረደባቸው አንዳንዶቻችን የምናስታውሰው ነው። ደግነቱ እንደዚህ ያሉ መረን የለቀቁ ትችቶች እንደተፈራው በአገሪቱ ታሪክ ጉልህ ሚና የነበራቸው ሰዎች ትውስታቸውንና ትዝታቸውን ከማካፈል አላገዱም። እንዲያውም በአሁኑ ጊዜ መድረኩን በከፍተኛ ደረጃ የተቆጣጠሩት እንዲህ ዓይነት መጻሕፍት እየሆኑ መጥተዋል።

የታሪክ ባለሙያዎች ትውስታዎችን የሚመለከቱበት ሳይንሳዊ መንገድ አላቸው። እነሱን የሚያዩዋቸው እንደ ታሪክ ሳይሆን ታሪክ ለመጻፍ እንደሚረዱ አጋዥ ሰነዶች ነው። በተለይም አወዛጋቢ በሆኑ የታሪክ ክስተቶች ውስጥ ዐቢይ ሚና የነበራቸው ተዋንያን ገድላቸውን አግዝፈው፣ ስሕተቶቻቸውን አድበስብሰው ወይም ደብቀው ስለሚጽፉ በከፍተኛ ጥንቃቄ ነው መያዝ ያለባቸው። ትውስታቸው በአብዛኛው በማስታወስ እንጂ በሰነድ ላይ የተመሠረተ ባለመሆኑም አንዳንዴ የመረጃ መዛነፍም ሊያጋጥም ይችላል።

በዚህ ረገድ የአምባሳደር እምሩ ዘለቀ ትውስታ በቅርቡ ለታሪክ ጥናት ግብዓት ሊሆን የሚችል መጽሐፍ ነው። አምባሳደሩ መጽሐፉን መጀመሪያ በእንግሊዝኛ ጽፈው በአሜሪካ አገር ያሳተሙት ሲሆን፤ እዚህ ለግምገማ የቀረበው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ያሳተመው የአማርኛው ቅጂ ነው። በ99 ዓመታቸው በጥቅምት 2015 ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት አምባሳደር እምሩ ከስመ ጥር ቤተሰብ ተወልደው ደማቅ ዲፕሎማሲያዊና ፖለቲካዊ ሕይወት ለመኖር የቻሉ ኢትዮጵያዊ ናቸው።

የደራሲው አባት በጅሮንድ ዘለቀ አግደው በፈረንሣይና በመንግሥታቱ ማኅበር (League of Nations) ዘንድ የኢትዮጵያ አምባሳደር የነበሩ ሲሆን፣ አያታቸው ነጋድራስ አግደው እምሩ ደግሞ አዲስ አበባ እንደተቆረቆረች የመጀመሪያው ነጋድራስ ነበሩ። ደራሲው በለጋ ዕድሜያቸው ከሚያካፍሉን ትውስታዎች በዋነኛነት ሊጠቀሱ የሚችሉት የተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ቆይታቸው እና የየካቲት 12 1929 የግራዚኒ እልቂት ነው። ስለ ትምህርት ቤቱ የሚያካፍሉን መረጃ ከሌሎች የዘመኑ ተማሪዎች ትውስታ (ለምሳሌ የአቶ አማኑኤል አብርሃም *የሕይወቴ ትዝታ*፣ 1992) ጋር በመዳበል ስለ ትምህርት ቤቱ የተሟላ ስዕል ለማግኘት ይረዳናል።

እንደዚሁ ስለ የካቲት 12ቱ እልቂት በልጅነት አእምሯቸው (ያኔ ዕድሜያቸው ገና 14 ዓመት ነበር) ያዩትና የታዘቡት ሁኔታም ተመስገን ገብሬ *ሕይወቴ* በተሰኘው ግለ ታሪኩ እንደሚዘግበው እጅግ ስዕላዊ ባይሆንም ያቺን የሰቆቃ ቀን ለመረዳት የራሱን አስተዋጽኦ ያደርጋል። ጨቅላ ዕድሜያቸው ግን መጀመሪያ በአቃቂ "ማጎርያ ጣቢያ"፣ ቀጥሎ ደግሞ ሶሚሊያ በሚገኘው ደናኔ በሚገኘው እስር ቤት ከአያሌ ኢትዮጵያውያን ጋር እስከ ጥር 1932 ታግተው ከመቆየት አላዳናቸውም። በዚህ አጋጣሚም ደራሲው ስለ ደናኔ እስር ቤት የውስጥ ሁኔታ ሌላ ቦታ የማናገኘው ብርቅ መረጃ ያካፍሉናል።

ምናልባትም የመጽሐፉ ትልቁ ፋይዳ በድኅረ-ነፃነት ማግስት ኤርትራን ወደ ኢትዮጵያ ለማስመለስ ስለተደረገው ዲፕሎማሲያዊ ትግል በሚሰጠው ተጨማሪ መረጃ ነው። በዚህ ረገድ በምክትል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አክሊሉ ሀብተ ወልድ መሪ ተዋናይነት ስለተደረገው እልህ አስጨራሽ ተጋድሎ አምባሳደር ዘውዴ ረታ *የኤርትራ ጉዳይ* በተሰኘው መጽሐፋቸው ለአንባብያን ከፍተኛ ግንዛቤ ማስጨበጣቸውን ሁላችንም የምናውቀው ጉዳይ ነው። ሌላው አምባሳደር (እምሩ) ደግሞ በዚህኛው መጽሐፍ አማካይነት ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎች ያካፍሉናል። በለንደንና ፓሪስ በተካሄዱት ጉባዔዎች ላይ የኢትዮጵያ ልዑክ አባል ሆነው የተሳተፉ በመሆናቸው ሂደቱን በቅርብ መከታተል ችለዋል። በተለይም ኢትዮጵያ የይገባኛል ጥያቄዋን ለማጠናከር ስላዘጋጀችው ‹‹ግሪን ቡክ›› ዘርዘር ያለ መረጃ ያካፍሉናል፡ ይህ እጅግ ታሪካዊ የሆነ ሰነድ ኢትዮጵያ ከታሪክና ከኅልውናዋ አንፃር ኤርትራ እንድትመለስላት የሚያስፈልግበትን ምክንያት በዝርዝር ከማቅረቡም በላይ፤ ይህንኑ ለማጠናከር በወቅቱ በተለያዩ የኢትዮጵያ መንግሥት መሥሪያ ቤቶች በኃላፊነት የሚሠሩትን ኤርትራውያን እና በፋሽስት ወረራው ወቅት ከኢትዮጵያውያን ጎን ተሰልፈው የተፋለሙትን ኤርትራውያንም ስም ዝርዝር የያዘ ነው።

ሌላው መጽሐፉ የሚፈነጥቅልን ሁኔታ የአክሊሉ ሀብተ ወልድን ሰብዕና የተመለከተ ነው። ለአብነትም ደራሲው አክሊሉ የተጻፈ ከማንበብ ይልቅ ያለ ዝግጅት መናገር ይቀናቸዋል ይሉናል። በእርግጥም ይህ አገላለጽ በአንድ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ስብሰባ ወቅት የሶማሌው ፕሬዚዳንት ኢትዮጵያን ወቅሶ ላደረገው ንግግር ከመቅጽበት ያለ ምንም ዝግጅት የሰጡትን ታሪካዊ መልስ ያስታውሰናል። በአንጻሩ በዚሁ በኤርትራ ጉዳይ በለንደን በተካሄደው ጉባዔ ላይ 86 ገጽ ያለው ሪፖርት በንባብ ማሰማታቸው ምንም እንኳን እንደ ታላቅ ገድል የሚቆጠር ቢሆን፣ የርሳቸው ዘገምተኛ አንባቢነትና የወቅቱ የአየሩም ሙቀት ታክሎበት አድማጮቹን በብርቱ እንደ ፈተናቸው

ይገልጹልናል (159)፡፡ ሌላው ደራሲው የሚሰጡን መረጃ ደግሞ በአክሊሉና በጽሕፈት ሚኒስትሩ ጸሐፌ ትእዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ መካከል  ኤርትራን በማስመለሱ ረገድ የነበረው የታሪክ ሽሚያ ነው (242)፡፡ እንዲሁም የማታ ማታ ብዙ ጠንቅ ላስከተለው የፌዴሬሽኑ መፍረስ መንግሥትንም የኤርትራ የአንድነት ኃይሎችንም እኩል ተጠያቂ ያደርጓቸዋል፡፡

ሌላው የመጽሐፉ ፋይዳ ደራሲው በተለያዩ አገራት በአምባሳደርነት ስላገለገሉበት የሚያካፍሉን ትውስታ ነው፡፡ በዚህም ረገድ መጀመሪያ የተሰየሙት ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ በጀርመን አገር ነው፡፡ ለርሳቸው የመጀመሪያው ምደባ የሆነውን ያህል ለኢትዮጵያም በጀርመን አገር አምባሳደር ስትሰይም የመጀመሪያው መሆኑ ነው፡፡ በዚህም ሁኔታ አዲሱ አምባሳደር የአገሪቱን የድኅረ-ጦርነት ሁኔታ ከመተረካቸው ባሻገር የንጉሠ ነገሥቱን የ1946 ታሪካዊ ጉብኝት በዝርዝር ይገልፁልናል፡፡ የጉብኝቱ ታሪካዊነት ጀርመን በጦርነቱ ቁርሾ ምክንያት ከዓለም በተገለለችበት ወቅት አገሪቱን በመጎብኘት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የመጀመሪያው የውጭ አገር መሪ በመሆናቸው ነው፡፡ ይህም በጀርመኖች ዘንድ እንደ ትልቅ ውለታ ተቆጥሮ እስከ አብዮቱ ዘመን ድረስ ኢትዮጵያውያን ቪዛ ሳያስፈልጋቸው ጀርመን አገር እንደ ልባቸው መግባት እንዲችሉ አስችሏቸዋል፡፡ ከዚያም በኋላ ደራሲው በጋና እና በስዊድን አምባሳደር ሆነው አገልግለዋል፡፡ በኋለኛው ምድባቸው መጀመሪያ ያጋጠማቸው ክስተት፣ ምንም እንኳን በወቅቱ እዚያ ባይኖሩም፣ ኤምባሲው ስዊድን አገር በሚኖሩ ተማሪዎች መወረሩ ነበር፡፡ ይህ በ1961 የተከሰተው አጠቃላይ የኢትዮጵያ ተማሪዎች አመፅ ነፀብራቅ ነበር፡፡

ደራሲው ከንጉሣውያን ቤተ ሰብ በአጠቃላይ፣ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር በተለይ፣ ልዩ ቀረቤታ ነበራቸው፤ ምንም እንኳን የቤተ መንግሥቱን ፖለቲካ ‹‹ቢዛንታይን›› ወይም ‹‹ካፍካዊ›› ብለው ለመግለፅ ቢገደዱም፡፡ በተለይም ከሐረሩ መስፍን ልዑል መኰንን ጋር ልዩ ትስስር ነበራቸው፡፡ ባለቤታቸውን ልዕልት ሣራ ግዛውንም ‹‹ሳባዊ ውበት›› (234) የተጎናፀፉ ሲሉ ይገልጿቸዋል፡፡ ደራሲው የመስፍኑ የግል ጸሐፊ ሆነው ተመድበው በሐረር ከሰጡት አገልግሎት ባሻገር መስፍኑ የአንድነት ኃይሎችን ለማጠናከር ወደ ኤርትራ ሲላኩ አጅበዋቸው ሄደዋል፡፡ ስለ መስፍኑ እስካሁን እምብዛም የማናውቃቸውን ባሕርያት ያጋሩናል፡- ስለ ዘመናዊ አስተሳሰባቸው፣ ለሕዝብ ጉዳይ ተቆርቋሪ ስለመሆናቸው እና ስለ አባታቸው መንግሥት አካሄድ ያደረባቸው ስጋት፡፡ አሟሟታቸውን በተመለከተም በስፋት ተዛምቶ የነበረውን በቀናተኛ ባል ነው የተገደሉት የሚባለውን ወሬ ፍጹም መሠረት እንደሌለውና የሞቱት በዜና እንደተነገረው በመኪና አደጋ መሆኑን አስረግጠው ይነግሩናል፡፡

ደራሲው ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር በተለያዩ አጋጣሚዎች ለመነጋገርና ሰብዕናቸውንም በቅጡ ለመረዳት ዕድል አግኝተዋል፡፡ ይህን ሰብዕናቸውንም በሚከተሉት ቃላት ነው የሚገልጹት፡፡-

> አጠቃላይ ባህርያቸው ቀለል ያለ ቢሆንም - ትህትና የተላበሰ ሊባልም ይችላል - ሰብዕናቸው ከፍተኛ ድባብና ግርማ ሞገስ የሚንጸባረቅበት ነበር፡፡ ፈገግታቸው በጣም የሚስብ ነበር፤ በሰው ዘንድ የደስደስና ተወዳጅነት ነበራቸው፡፡ የተለያዩ የውጭ አገር ሰዎች ስለ እሳቸው በቀላሉ የሞቀ ስሜት ይሰማቸው ነበር፡፡ ይህም ሆኖ ከለስላሳ አመለካከታቸው ሥር ቁርጠኛ ባሕርይ እንዳላቸው፤ ለጨበጡት ሥልጣንና ጥቅማጥቅም ቀናኢ መሆናቸውን ለይቶ ማየት ይቻል ነበር፡፡ (228)

በምዕራፍ 20 ይህን የንጉሠ ነገሥቱን ሰብዕና ከአስተዳደጋቸው ጋር በማጣመር አብራርተው ጽፈውታል፡፡ በተለይም አባታቸው ራስ መኰንን ከሞቱ በኋላ በአደራነት የከበቧቸው ወግ አጥባቂ ታማኞኛቸው ባሳደሩት ተጽእኖ ሳቢያ ‹‹በሀያኛው ክፍለ ዘመን ዓለም ውስጥ እየኖሩ የተጐናጸፉት ግን የአሥራ አምስተኛውን ክፍለ ዘመን መንግሥታዊ የፖለቲካና የማኅበራዊ ባህል ነበር›› ይሉናል፡፡ በዘመነ መንግሥታቸው የተከናወኑትን ተግባራት ከዘረዘሩልን በኋላ ‹‹በአንድ ሰው ብቻ እንደሚመሩት ሌሎች አገዛዞች ሁሉ ያሁኑን ዘመን ሊያገለግሉ የሚችሉ ጠንካራ የሆኑ የፖለቲካ ተቋሞችን አልገነቡም፤ ይኸውም እሳቸውን ሊገዳደሩ ይችላል ከሚል ፍራቻ የተነሳ ሊሆን ይችላል›› (265) በማለት ሕፀፃቸውንም ይጠቁማሉ፡፡

ደራሲው ከነበራቸው ጉልህ መንግሥታዊ ተሳትፎ መካከል ሕገ መንግሥቱን በማሻሻል ሂደት ለዚሁ ጉዳይ የተመደበው ኮሚቴ ጸሐፊ ሆነው ማገልገላቸው ተጠቃሽ ነው፡፡ ኮሚቴውን የሚመሩት የወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ራስ ቢትወደድ መኰንን እንዳልካቸው ሲሆኑ፤ አባላቱም ራስ አበበ አረጋይ፣ ጸሐፌ ትእዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ፣ አቶ መኰንን ሀብተ ወልድ፣ ልጅ ይልማ ዴሬሳ እና ብላታ ዘውዴ በላይነህ ነበሩ፡፡ በተጨማሪም በአማካሪነት የውጭ አገር ሰዎችም ነበሩ፡፡ በጸሐፊነታቸው ብዙ ሰነዶችንና ጥቆማዎችን መመርመርና ለኮሚቴው ማቅረብ ስለነበረባቸው ምን ያህል አድካሚ እንደነበር ይጠቁሙናል፡፡ በዚህ ረገድ በተለይ ከልዑል ራስ ካሣ እና ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ያደረጓቸው ውይይቶች ቀልብ የሚስቡ ናቸው፡፡ አፍቃሬ እንግሊዝ የሆኑት ራስ ካሣ ‹‹ከእንግሊዙ ሕገ መንግሥት ጋር ተመሳሳይ አድርጉት ብለህ ንገራቸው›› ብለው አስተያየት ሲሰጡ ደራሲው እንግሊዝ ሕገ መንግሥት እንደ ሌላት ማስረዳት ነበረባቸው፡፡ በሌላ ወቅት ደግሞ ንጉሠ ነገሥቱን ‹‹ሥዩመ እግዚአብሔር›› ብሎ የሚጠቅሰው ሐረግ እንዲወጣ ንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ጥያቄውን እንዲያቀርቡ በጸሐፊነታቸው ተፈርዶባቸው ይህንኑ ሲነግሯቸው

የሚከተለውን መልስ ያገኛሉ፡- ‹‹እግዚአብሔር ባይፈቅድ ኖሮ ይህንን የሥልጣን ቦታ ለመያዝ እንዴት እችል ነበር ብለህ ታስባለህ?›› ሌላው ሕገ መንግሥቱን በማሻሻል ሂደት ደራሲው የሚያጋሩን ነገር ሲቪክ መብቶችን የሸበበው ‹‹[ሕጉ] በሚፈቅደው መሠረት›› የሚለውን ሐሳብ ያመነጩት አክሊሉ ሀብተ ወልድ እንደነበሩ ነው።

ከመንግሥት አገልግሎት ውጪም ደራሲው ጉልህ የሆነ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ተሳትፎ ነበራቸው ማለት ይቻላል። በጨለማው የኢጣልያ ፋሽስት አገዛዝ ዘመን ሕይወታቸውን ፈካ ያደረገላቸው ከሐኪም ወርቅነህ እና ከከንቲባ ገብሩ ቤተሰቦች ጋር የነበራቸው ቅርርብ ነበር። ከነሱም መካከል ከአቶ ይልማ ዴሬሳ (የሐኪም ወርቅነህን ልጅ ኤልሳቤጥን ያገቡት)፣ አቶ መኩሪያ ወልደ ሥላሴ (የእሌኒ መኩሪያ አባት፣ ሌላዋን የሐኪም ወርቅነህን ልጅ ሱዚን ያገቡት) እና አቶ በፈቃዱ ወልደ ሚካኤል ጋር በየቀኑ እየተገናኙ ‹‹የተጧጧፈና ደስ የሚል›› ውይይት ያደርጉ ነበር። ያኔ ግን ደራሲው ገና ሃያ ዓመት ያልሞላቸው ጉብል ስለነበሩ ከአዳማጭነት የዘለለ ሚና ነበራቸው ብሎ ለመገመት ያዳግታል። በተጨማሪም ውጭ አገር ተምረው የተመለሱ ኢትዮጵያውያን መርካቶ በሚገኘው የአቶ ተስፋዬ ቀጀላ የነበረው ቡና ቤት እየተገናኙ ይወያዩ እንደ ነበር ይነግሩናል። አንዳንዶቹም በውስጥ አርበኝነት የነፃነት ትግሉን ያግዙ ነበር። ከነፃነት መልስ በአርበኞችና በስደተኞች መካከል ስለነበረው የቡድን ሽኩቻም ተጨማሪ መረጃ ያጋሩናል። በተለይም የመጀመሪያዎቹ ለጠቅላይ ግዛት አስተዳዳሪነት፣ ሁለተኞቹ ደግሞ ለሚኒስትርነት ይመረጡ እንደነበር ይጠቁሙናል። የማዕከላዊ መንግሥት ሥልጣኑም በጸሐፌ ትእዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ እና በአጋራቸው በአቶ መኰንን ሀብተ ወልድ ጥምረት ሲካሄድ፤ እነ አሸብር ገብረ ሕይወትን የመሰሉት ከመንግሥት ሥልጣን አካባቢ እንደተገለሉ፣ እንደ መኰንን ደስታ ያሉት ደግሞ ስሕተት ሰርታችኋል በመባል እንደሚሻሩ ወይም በአምባሳደርነት ወደ ውጭ አገር እንደሚላኩ ይነግሩናል።

ደራሲው ራሳቸው የፖለቲካ ተሳትፏቸው እያደገ እንደሄደ እንረዳለን። በመጀመሪያ ደረጃ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር የሚያደርጉት ውይይት ድፍረት የተሞላበት ነበር። ከዚያም ከድፍረት ወደ ተቃውሞ ተሸጋግሮ በተለይ ንጉሠ ነገሥቱን ከአንዴም ሁለቴ ከተጋፈጡት ከደጃዝማች ታከለ ወልደ ሐዋርያት ጋር ሲያብሩ እናገኛቸዋለን። የእነ ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ከመካሄዱ ከሁለት ዓመት በፊት (በ1951 ዓ.ም.) ሁለቱ የፖለቲካ ፓርቲ እስከማቋቋም ይደርሳሉ። ደጃዝማቹ የፓርቲው ሊቀ መንበር፣ ደራሲው ምክትል ሊቀ መንበር ሲሆኑ ከአባላቱ መካልም በርዕዮተ ዓለም አመለካከቱ መጠቅ የሚለው አቶ ሥዩም ስብሐት ይገኝበት ነበር። የፓርቲው ስም በሚያስገርም ሁኔታ (የኋላውን ክስተት ስናጤን) የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ፓርቲ (ኢዴፓ) ነበር። ከአብዮት በኋላም በኒው ዮርክ በአንድ ባንክ ውስጥ የነበራቸውን የተደላደለ ሥራ ትተው ለጥቂት ጊዜ የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ኅብረትን (ኢዴህ ወይም ኢዲዩ) ተቀላቅለዋል። ይሁን እንጂ በአመራሩ መካከል የነበረው ክፍፍል ትግሉን የሚያራምድ አለመሆኑን ሲረዱ ወደ አሜሪካቸው ተመለሱ።

የአምባሳደር እምሩ ዘለቀ መጽሐፍ ከላይ እንደተመለከተው ስለ ጣልያን ወረራ ወቅት እና ስለ ድኅረ-ነፃነት ኢትዮጵያ ጠቃሚ መረጃዎችን የሚሰጠን ሲሆን፤ አንዳንድ ጉድለቶች አልታጡበትም። ከነዚህም መካከል በተለይ የአብዮቱን ሂደት የሚገልጹበት መንገድ ቁንጽል መሆኑ ነው። የእድገት በኅብረት ዘመቻን በተመለከተም አሉታዊ ጎኑ ላይ ብቻ ለማተኮር መርጠዋል። ስለ ኢሕአዴግ አባል ድርጅቶች የሚሰጡት መረጃም የተዛነፈ ነው። ሌላው የመጽሐፉ ጉድለት እንደዚያ የረጅም ዘመን ሕይወትን ለሚተርክ መጽሐፍ በምስል ድርቅ መጠቃቱ ነው። ሰባት ስምንት ዐሠርት ለፈጀ ደማቅ ሕይወት ላሳለፉ ባለ ታሪክ 18 ብቻ ምስሎች ማቅረቡ ታሪኩን አይመጥነውም። የስዕሎቹ መግለጫዎች (ካፕሽኖች) ደግሞ በየምስሉ ግርጌ በመስፈር ፈንታ በማውጫ መልክ በመጽሐፉ መጀመሪያ ላይ መደርደራቸው አንባቢውን ለአላስፈላጊ ድካም ይዳርጋል።

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ ይህን እጅግ ጠቃሚ የሆነ መጽሐፍ ማሳተሙ የሚያስመሰግነው ሲሆን፤ የኅትመቱ ጥራት ግን ከዚህ ቀደም ካሳተማቸው መጻሕፍት ደረጃ ዝቅ ያለ ነው። በአጠቃላይ መጽሐፉ በችኮላ የታተመ ይመስላል። በሚቀጥሉት ኅትመቶች በመጀመሪያው እትም የታዩት ሕፀፆች ተስተካክለው ይቀርባሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

ባሕሩ ዘውዴ (ኤመሪተስ ፕሮፌሰር)

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ